# እንውጣ ራስ ዳሽን

**በሰለሞን ሽፈራው**

በሞት ሽረት ትግል ጉዞ ውጣ ውረድ፣
ለህዳሴው ዘመን፣ ጥሮ አትራፊ ትውልድ
አባ ጽናት መሌ፣ የቀየሰው መንገድ
የሩቅ ህልሙ ትልሙ፣ ፈር እንዳይንጋደድ
በደም ባጥንታችን፣ ውህደት የነደቅነው
የአንድነት ዓፀድ፣
እያደር ደርጅቶ፣ በመካከላችን
ፍቅር ስሩን ሲሰድ
ተረት ሆኖ እንዲቀር፣
ድህነት አመጣሽ፣ የኛ ቤት ጨለማ
የኢትዮጵያ ህዝቦች፣ አብረን በቀመርነው
ህብረ*-ብሄር ዜማ
ክተት ተጠራርተን፣ ገጠር ተከተማ
በገዛ ራስ ጥረት፣ ዓባይን ገድበን
ሀገር ልናለማ
የማይቀለበስ፣ ቃል መግባታችንን
ዓለም እንዲሰማ
ኑ እንውጣ ራስ ዳሽን፣ ከረጅሙ ማማ፡፡

ታላቋ መሪያችን፣ በወጋልን ዳና

ለተስፋይቱ ምድር፣ ዕድገት ብልጽግና

አብረን ተነባብረን፣ በልማት ጎዳና

የሩቅ ህልሙም ትልሙም፣ እንዳይቀለበስ

መለስ ባወረሰን፣ ድል አድራጊ መንፈስ

የፀረ ድህነት፣ ትግሉን ዳር ለማድረስ

መላው ደቡብ ህዝቦች፣ኦሮሚያ ሶማሌ

ሐረሪ ጋምቤላ፣ አፋር አባጊሌ

ጉምዝና ቤንሻንጉል፣ ትግራይና አማራ

ታላቋ መሪያችን፣ ለሰጠን አደራ

ለህዳሴው ዘመን፣ ያባይ ዳር ሙሽራ

ለተስፋይቱ ምድር፣ ታሪክ ልንሰራ

የኢትዮጵያ ልጆች፣ አብረን-ተነባብረን፣

ቆመናል በጋራ፡፡

የባህል የቋንቋ፣ የዘር የሃይማኖት

ህብር ባደመቀው፣ ጤናማ ልዩነት

የቅድስት ሀገር፣ ምስጢረ-መለኮት

ውበት ተጎናጽፎ፣ ለዓለመ ዓለም

በሚገለጽበት

የህዳሴው ዘመን፣ ኢትዮጵያዊነት....

እኛው መክረን ዘክረን፣ በራስ መፈቃቀድ

ከደም ካጥንታችን፣ ውህደት በነደቅነው

የማንነት ዓፀድ....

ለዕልፍ አዕላልፍ ህዝቦች፣ ጥምር ልዕልና

በህገ-መንግስቱ፣ ታምነን ልንጸና
የማይቀለበስ፣ ቃል ገብተናልና…
ታላቁ መሪያችን፣ ባሰመረው ፈለግ
የሩቅ ህልሙን ትልሙን፣ ዕውን እስክናደርግ
አባ ፅናት መሌ፣ ዕድሜ ልኩን ታግሎ
ባወረሰን ራዕይ «ዳር አድርሱት» ብሎ
የህዳሴያችንን፣ ጉዞ ለማሳካት
አብረን-ተነባብረን፣ ቆመናል በትጋት፡፡
ነገር አያያዙን፣ እኛ ካወቅንበት
የባህል የቋንቋ፣ የዘር የሃይማኖት
ህብር ያደመቀው፣ ጤናማ ልዩነት
ጌጣችን ነውና፣ ኢትዮጵያዊ ውበት
ታላቁ መሪያችን፣ በሰጠን አደራ
አብረን-ተነባብረን፣ እንደ ባለተራ
የትንሳኤ ዳግም፣ ታሪክ ልንሰራ
ለህዳሴው ዘመን፣ ያባይዳር ሙሽራ
ለተስፋይቱ ምድር፣ ቆመናል በጋራ፡፡
የኢትዮጵያ፣ ህዝቦች
አብረን-በቀመርነው፣ ህብረብሄር ዜማ
ክተት ተጠራርተን፣ ሀገር ስናለማ
ተረት ሆኖ እንዲቀር፣ ድህነት ጨለማ
ኑ እንውጣ ራስ ዳሽን፣ ከተራራው ማማ
ለዓለመ ዓለም፣
የዳግም ልደትን ብስራት ልናሰማ

ሰለሞን ሽፈራው

ህዳር/2005 ዓ.ም አዲስ አበባ

ስልክ ቁጥር 0924372048